# <u>የእጩ ተወዳዳሪዎች ወኪሎች የፍቃድ አሰጣጥ፣ የአሰራር እና የሥነ-ምግባር መመሪያ ቁጥር 17/2013 ዓ.ም</u>

## <u>ምዕራፍ አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

**አንቀፅ 1. <u>አውጪው ባለስልጣን</u>**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀፅ 120 ንኡስ አንቀፅ (5) መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

**አንቀፅ 2. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ መመሪያ "የእጩ ተወዳዳሪዎች ወኪሎች የፍቃድ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 17/2013 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**አንቀፅ 3. <u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"እጩ ተወዳዳሪ"** ማለት በምርጫ ለመወዳደር በፖለቲካ ፓርቲ ወይም በግሉ የተመዘገበ ሰው ነው።
2. **"የእጩ ወኪል"** ማለት አንድን የፖለቲካ ፓርቲ በመወከል ወይም በግሉ ምርጫ ላይ ለመወዳደር በእጩነት የተመዘገበ እጩ ተወዳዳሪ በምርጫ ጣቢያ ወይም በምርጫ ክልል ላይ በሚደረጉ የምርጫ ሂደቶች ላይ የወከለው እጩ ተወዳዳሪ መብት መከበሩን የሚከታተል ሰው ነው።
3. **"ተጠባባቂ ወኪል"** ማለት የእጩ ተቀማጭ ወይም ተዘዋዋሪ ወኪል ሲጓደል ተክቶ የሚሰራ የእጩ ወኪል ነው።
4. **"ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት"** ማለት በማንኛውም መደበኛ ሁኔታ ይደርሳሉ ተብሎ ያልተገመቱ እና ያልተጠበቁ ከአመልካቹ ቁጥጥር ውጪ በሆነ ምክንያት የሚደርሱ እና እንዳይደርሱ መከላከል ወይም ማስቆም የማይቻሉ ክስተቶች ናቸው።
5. የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 እና በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 ላይ የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ያገለግላሉ።

**አንቀፅ 4. <u>የፆታ አገላለፅ</u>**

በዚህ መመሪያ ላይ በአንደኛው ፆታ የተደነገገው አነጋገር ሌላኛውንም ፆታ ያካትታል።

**አንቀፅ 5. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

1. ይህ መመሪያ በማንኛውም ጠቅላላ ምርጫ፣ የአካባቢ ምርጫ፣ ድጋሚ ምርጫ፣ እና ማሟያ ምርጫ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።
2. ይህ መመሪያ አስፈላጊ የሆኑ የአተረጓጎም ለውጦች ተደርገውበት በህዝበ ውሳኔ ላይም ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል።

**አንቀጽ 6. <u>አላማ</u>**

የዚህ መመሪያ አላማ በአዋጁ መሰረት የፓለቲካ ፓርቲ እና የግል እጩዎች በወኪሎቻቸው አማካኝነት የምርጫውን ሂደት የመከታተል፣ መረጃ የማግኘት እና አቤቱታ የማቅረብ መብታቸውን እንዲጠቀሙ ለማስቻል የወኪሎች ፍቃድ አሰጣጥ ሥርዓትን እና ሥነ-ምግባር መዘርጋት ነው።

## <u>ምዕራፍ ሁለት</u>

## <u>የእጩ ወኪሎች አይነት እና ፍቃድ አሰጣጥ</u>

**አንቀፅ 7. <u>የወኪልነት መመዘኛዎች</u>**

የእጩ ወኪል መሆን የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡

1. ኢትዮጵያዊ ዜጋ የሆነች፣
2. እድሜዋ 21 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆነች፣
3. የመምረጥ እና መመረጥ መብቷ በሕግ ያልተገደበ፣
4. የታወቀ ብልሹ ስነ-ምግባር የሌለባት፣
5. ማንበብ እና መፃፍ የምትችል እና
6. በእጩ ተወዳዳሪነት ያልተመዘገበች መሆን አለባት።

**አንቀፅ 8. <u>ስለወኪሎች አይነት</u>**

1. ማንኛውም እጩ ያቀረበ የፖለቲካ ፓርቲ እና የግል እጩ የምርጫ ሂደትን የሚከታተሉ ተቀማጭ እና ተዘዋዋሪ ወኪሎችን በሚወዳደሩበት የምርጫ ክልል እና የምርጫ ጣቢያዎች ሊሰይም ይችላል።
2. ከላይ በንኡስ አንቀፅ (1) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ እጩ ያቀረበ የፖለቲካ ፓርቲ እና የግል እጩ የጎደለ ተቀማጭ ወይም ተዘዋዋሪ ወኪልን በመተካት የምርጫ ሂደትን የሚመለከቱላቸው ተጠባባቂ ወኪሎች ሊኖራቸው ይችላል።

**አንቀፅ 9. <u>የተቀማጭ ወኪሎች አመዳደብ</u>**

ማንኛውም እጩ ያቀረበ የፖለቲካ ፓርቲ እና የግል እጩ የምርጫ ሂደትን የሚከታተሉ፤

1. ለሚወዳደርበት የምርጫ ክልል ሁለት እየተቀያየሩ የሚሰሩ ተቀማጭ ወኪሎች፣
2. በሚወዳደርበት የምርጫ ክልል ስር ላሉ የምርጫ ጣቢያዎች ለእያንዳንዱ እየተቀያየሩ የሚሰሩ ሁለት ተቀማጭ ወኪሎች መመደብ ይችላል፤ቢያንስ አንዷን ሴት እንዲያደርጉ ይበረታታሉ።

**አንቀፅ 10. <u>የተዘዋዋሪ ወኪሎች አመዳደብ</u>**

1. እያንዳንዱ እጩ ያቀረበ የፖለቲካ ፓርቲ እና የግል እጩ ተወዳዳሪ በሚወዳደርበት የምርጫ ክልል ከሰባት የማይበልጡ ተዘዋዋሪ ወኪሎች መመደብ ይችላል።
2. ከሚመድባቸው ተዘዋዋሪ ወኪሎች ቢያንስ አንዷን ሴት እንዲያደርግ ይበረታታል።

**አንቀፅ 11. <u>የወኪሎችን ዝርዝር ስለማሳወቅ</u>**

1. ማንኛዋም የግል እጩ የተቀማጭ እና የተዘዋዋሪ ወኪሎቹን እና የተጠባባቂ ወኪሎቹን ስም ዝርዝር የመጀመሪያ/ጊዜያዊ የእጩዎች ዝርዝር በምርጫ ክልል ይፋ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ድምጽ መስጫው እለት ሰባት ቀን እስኪቀረው ድረስ በማንኛውም ጊዜ ለምርጫ ክልል ጽ/ቤት ማቅረብ ትችላለች።
2. ማንኛውም እጩ ያቀረበ የፖለቲካ ፓርቲ በሚወዳደርበት የምርጫ ክልል እና በዚሁ ክልል ውስጥ ለሚገኙ እያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ የተቀማጭ እና ተዘዋዋሪ ወኪሎችን ዝርዝር ለብሔራዊ ምርጫ ቦርዱ ዋና መስሪያ ቤት ሊያቀርብ ይችላል።

3. የምርጫ ክልሉ ጽ/ቤት ዝርዝር በቀረበለት በሁለት ቀናት ውስጥ ለእያንዳንዱ ወኪል የወኪልነት መታወቂያ በማዘጋጀት ይሰጣል።
4. የምርጫ ክልሉ ጽ/ቤት የእያንዳንዱ እጩ ተቀማጭ፣ ተጠባባቂ እና ተዘዋዋሪ ወኪል ዝርዝርን የሚገልፅ ደብዳቤ በምርጫ ክልሉ ውስጥ ላሉ የምርጫ ጣቢያዎች ከድምጽ መስጫ ቀን በፊት ከ3-5 ቀናት መላክ አለበት።
5. የእጩ ወኪሎችን ዝርዝር በሚያቀርቡበት ወቅት በተቻላቸው መጠን የፆታ ተዋፅኦ ለማመጣጠን ጥረት በማድረግ ዝርዝሩን በፆታ ለይተው ማቅረብ አለባቸው።

**አንቀፅ 12. <u>የወኪሎችን ዝርዝር በተቀመጠው የጊዜ ገደብ አለማሳወቅ</u>**

1. የወኪሎቹን ዝርዝር በአንቀፅ 11 ንኡስ አንቀፅ (1) በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ ያላሳወቀ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል ዕጩ ወኪል ማቅረብ እንዳልፈለገ ተደርጎ መብቱ ይታለፋል።
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ (1) ላይ የተጠቀሰው ቢኖርም የፖለቲካ ፓርቲው ወይም የግል እጩዋ የወኪሎችን ዝርዝር ያላቀረቡት ከአቅም በላይ በሆነ አሳማኝ ምክንያት መሆኑን ማስረዳት ከቻሉ ቦርዱ ወኪሎቹን አቅርባ እንዲታዘዙላት ሊፈቅድ ይችላል።
3. የወኪሎች ዝርዝር ማቅረቢያ ጊዜ በምንም መልኩ የድምፅ መስጫው እለት አራት ቀን ከቀረው በኋላ ከሆነ ተቀባይነት አይኖረውም።

**አንቀፅ 13. <u>የወኪሎች ዝርዝር የሚቀርብበት አሠራር</u>**

1. በፖለቲካ ፓርቲ የሚቀርብ የወኪሎች ዝርዝር በፓርቲው ማህተም እና በፖለቲካ ፓርቲው ከፍተኛ አመራር ወይም በአካባቢው በሚገኝ የዞን ወይም የወረዳ የፖለቲካ ፓርቲ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይም ህጋዊ ወኪል ፊርማ የተረጋገጠ መሆን አለበት።
2. ወኪሎች ያቀረበችው የግል እጩ ተወዳዳሪ ከሆነች፣ ዝርዝሩ በእጩዋ ፊርማ ብቻ የተረጋገጠ መሆን ይኖርበታል።
3. እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል የእጩ ተወዳዳሪ የወኪሎችን ዝርዝር ሲያቀርቡ ወኪሎቹ የተመደቡበትን የምርጫ ጣቢያ እና ክልል ለይቶ በግልፅ በመፃፍ ማሳወቅ አለባቸው።

## ምዕራፍ ሶስት

## የወኪል መብት፣ ግዴታ እና ሃላፊነት

### አንቀፅ 14. የእጩ ወኪሎች መብቶች

1. ማንኛዋም የእጩ ተቀማጭ ወኪል በተመደበችበት የምርጫ ጣቢያ የምርጫውን ሂደት የመከታተል፣ ተገቢ መረጃን የማግኘት፣ ቅሬታን በየደረጃው ለተቋቋመ የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴን ጨምሮ ለሚመለከተው አካል የማቅረብ እና ውሳኔ የማግኘት መብት አላት።
2. ማንኛዋም የእጩ ተዘዋዋሪ ወኪል በተመደበበት የምርጫ ክልል የምርጫ ሂደት የመከታተል፣ ተገቢ መረጃ የማግኘት እና ከተቀማጭ ወኪሉ ጋር የመገናኘት መብት አላት።
3. ማንኛዋም የእጩ ተዘዋዋሪ ወኪል በተመደበችበት የምርጫ ክልል ምርጫ ሂደት ላይ ቅሬታ ሲኖራት፡ -

   ሀ) ለቅሬታ ምክንያት የሆነው ክስተት የተፈጠረበት ምርጫ ጣቢያ ላይ ተወካይ የሆነችለት ፓርቲ ወይም የግል እጩ ተቀማጭ ወኪል ያለው ከሆነ ሁለቱም በጋራ በመሆን ወይም ተቀማጭ ወኪሏ ብቻ ቅሬታዋን ወይም መስተካከል ያለበትን ጉዳይ በየደረጃው ማቅረብ ትችላለች።

   ለ) ለቅሬታ ምክንያት የሆነው ክስትት የተፈጠረበት ምርጫ ጣቢያ ላይ ተቀማጭ ወኪል የሌለ ከሆነ ተዘዋዋሪ ወኪሏ ቅሬታውን ራሷ ማቅረብ ትችላለች።
4. የማንኛውም የተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ ወኪል ያለምንም ተፅእኖ የተሰጣትን የውክልና ተግባር ያለተጽእኖ የማከናወን መብት አላት።

### አንቀጽ 15. የእጩ ወኪሎች ተግባር እና ኃላፊነት

ማንኛዋም የእጩ ወኪል፡

1. በጊዜ ሰሌዳው መሠረት ጥሪ ሲተላለፍላት የምርጫውን አጠቃላይ ሂደት በተመደበችበት ምርጫ ክልል ወይም የምርጫ ጣቢያ ጽ/ቤት፣ ከቦርዱ ወይም ከምርጫ ክልሉ የተሰጣትን የእጩ ወኪል ታዛቢነት መታወቂያ ይዛ በመገኘት ተቀማጭ ወኪል ሆና ትታዘባለች።
2. የምርጫውን ሂደት በሚመለከት የሚያዙ ቃለ ጉባኤዎች እንዲሁም የሚሞሉ ቅፆች ላይ በሚመለከተው ቦታ ላይ ትፈርማለች። የተለየ ሀሳብ ያላት ወኪል የሀሳብ ልዩነቷ ተመዝግቦላት እንድትፈርም ይደረጋል።

3. የሚሰጠውን መተማመኛም ሆነ ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሰነዶች ለወከላት ፓርቲ ወይም የግል ዕጩ ታደርሳለች።
4. በተመደበችበት የምርጫ ክልል ወይም የምርጫ ጣቢያ ጽ/ቤት የምርጫውን ሂደት ስትከታተል የሚያጋጥሟትን ቅሬታዎች ወዲያው እንደሁኔታው ለምርጫ ክልሉ ወይም ለምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በጽሁፍ ታቀርባለች።
5. የውክልና ስራዋን በሚመለከት ለወከላት የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል ዕጩ ትክክለኛ መረጃ መስጠት ይኖርባታል።

**አንቀፅ 16. <u>የተዘዋዋሪ ወኪሎች ተግባር እና ሃላፊነት</u>**

ማንኛዋም ተዘዋዋሪ ወኪል፣

1. የተሰጣትን የተዘዋዋሪ ወኪልነት መታወቂያ በግልፅ በሚታይ ሁኔታ ማንጠልጠል ይኖርባታል፤
2. በተመደበችበት የምርጫ ክልል ጽ/ቤት እና በስሩ የሚገኙ የምርጫ ጣቢያዎች ተዘዋውራ የምርጫ ሂደት መከታተል፣ ማየት እና አግባብ ያለው መረጃ መጠየቅ ትችላለች፤
3. በምትዘዋወርበት ወቅት ያጋጠማትን ቅሬታ በተከሰተበት የምርጫ ክልል ጽ/ቤት ወይም የምርጫ ጣቢያ ላይ ማቅረብ ትችላለች።

**አንቀፅ 17. <u>የተቀማጭ እና የተዘዋዋሪ ወኪሎች ግዴታ</u>**

ማንኛዋም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል ዕጩ ተቀማጭ ወይም ተዘዋዋሪ ወኪል፤

1. በየደረጃው ባሉ የምርጫ ሃላፊዎች የሚሰጠውን ትእዛዝ ማክበር አለባት፤
2. አግባብ ባለው አካል የወኪልነት መታወቂያ ስትጠየቅ ማሳየት እና መታወቂያዋን በግልጽ በሚታይ ሁኔታ ማንጠልጠል አለባት፤
3. ምርጫውን የሚያውኩ ተግባራት አለመፈፀም፣ አዋጁን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ማክበር እና ሌሎች በህግ የተከለከሉ ተግባራትን ከመፈጸም መቆጠብ አለባት፤
4. ማንኛዋም የእጩ ወኪል የምርጫውን አፈፃፀም ሂደት ከሚያደናቅፍ ማንኛውም ዓይነት ተግባር እና አካሄድ መቆጠብ ይኖርባታል፤
5. በምርጫ አስፈፃሚዎች ተግባር እና በውሳኔያቸው ጣልቃ መግባት ወይም የሚያጋጥሙ ችግሮችን በራሷ ለመፍታት መሞከር የለባትም፤

6. በምርጫ ጣቢያ ለመምረጥ ለተሰለፈው መራጭም ሆነ ድምፅ ለመስጠት ለሚሄደው መራጭ ሌላው መራጭ እገሌን መርጧል በማለት ወይም ሌላ ተመሳሳይ መረጃ በመስጠት መራጩን ሊያደናግር የሚችል ተግባር መፈፀም የለባትም።
7. መርጦ የሚመለስን መራጭ ማንን እንደመረጠ መጠየቅ የለባትም፤
8. የመራጮችን በሚስጥር ድምፅ የመስጠት መብት ማክበር አለባትበውክልና ከተመደበችበት ውጪ ምርጫን ለመታዘብ መንቀሳቀስ የለባትም፤
9. በማንኛውም ሁኔታ የምርጫ አስፈፃሚዎች ተግባር የሆኑትን መራጭን የማሰለፍ፣ የምርጫ ካርድን የመስጠት፣ በድምፅ መስጫው ወረቀት ላይ ማህተም የማድረግ፣ የምርጫ ካርድ እና የድምፅ መስጫ ወረቀት መቁጠር፣ መዝገብ ላይ ማስፈረም፣ ቀለም መቀባት፣ የምርጫ ሳጥን አካባቢ መዘዋወር፣ የምርጫ ሳጥንን መቆለፍ፣ መክፈት ወይም ማሸግና የመሳሰሉትን ተግባራት ማከናወን ወይም ምርጫ አስፈፃሚን በዚህ ረገድ ማገዝ ፈፅሞ የተከለከለ ነው።
10. የምርጫ ቅስቀሳ በተከለከለበት ጊዜ እና ቦታ መራጩ በተሰለፈበት ወይም በድምፅ መስጫው አከባቢም ሆነ በማንኛውም የምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ውስጥ እና 200 ሜትር ርቀት ክልል ውስጥ ቅስቀሳ ማድረግ የለባትም።
11. ለምርጫ አስፈጻሚዎች፣ ለአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት፣ ለሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የዕጩ ወኪሎች፣ ለመራጩ ህዝብ እና ለእጩ ተወዳዳሪዎች ተገቢውን ከበሬታ መስጠት እና ጨዋነት ማሳየት አለባት።
12. በተመደበችበት የምርጫ ክልል ወይም የምርጫ ጣቢያ ወገንተኝነትን የሚያንፀባርቁ ምልክቶችን፣ አርማዎችን ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ዕቃዎችን ይዞ ወይም ለብሶ መታየት ወይም በሰውነት እንቅስቃሴው የማንኛውም ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ ተወዳዳሪ ወገንተኝነትን የሚያንፀባርቅ ወይም የምርጫ ቅስቀሳ የሆነ ተግባር ማሳየት የለባትም።
13. የምርጫ ሂደት የሚከናወኑባቸው ቦታዎች ውስጥ እና ዙሪያ ላይ ማንኛውም ዓይነት የጦር መሳሪያ ታጥቃ መገኘት የለባትም።
14. የምርጫ እንቅስቃሴ በትክክል እና በቅልጥፍና እንዳይካሄድ ከሚያደርግ ማንኛውም ተግባር መቆጠብ አለባት።

15. የፖለቲካ ፓርቲ እና የግል ዕጩ ተቀማጭ እና ተዘዋዋሪ ወኪል ሆነ ብላ የምርጫውን ሂደት የሚያሰናክል ጥፋት ፈፅማ ከተገኘች አግባብ ባለው ህግ መሰረት ትቀጣለች።

**አንቀጽ 18. <u>የእጩ ወኪሎች መታወቂያ ካርድ አሰጣጥ</u>**

1. ማንኛውም እጩ ያቀረበ የፖለቲካ ፓርቲ ከምርጫ ቦርድ ዋና ጽ/ቤት ለተቀማጭም ሆነ ተዘዋዋሪ ወኪሎች የመታወቂያ ካርድ የሚሰጠው ሲሆን የግል እጩ ወኪሎች ከምርጫ ክልሉ ጽ/ቤት የሚቀበሉ ይሆናል።
2. የምርጫ ክልሉ በሕግ መሠረት አስፈላጊ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ የወኪሎች መታወቂያ ካርድ መስጠት ይኖርበታል።

**አንቀፅ 19. <u>የተጠባባቂ ወኪሎች ተግባር፣ ሃላፊነት፣ መብት እና ግዴታ</u>**

ተጠባባቂ ወኪሎች ተቀማጭ ወኪሎችን ተክተው በሚሰሩበት ወቅት ማንኛውም ተቀማጭ ወይም ተዘዋዋሪ ወኪል የሚኖረው ተግባር እና ሃላፊነት፣ መብት እና ግዴታ ይኖራቸዋል።

## <u>ምዕራፍ አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**አንቀፅ 20. <u>የወኪል አለመኖር</u>**

1. የማንኛውም ዕጩ ተዘዋዋሪም ሆነ ተቀማጭ ወኪል በራሱ ምክንያት በተመደበበት ቦታ ባልተገኘበት ወቅት የተካሄዱ የምርጫ ተግባራት ውድቅ እንዲደረግለት ሊጠይቅ አይችልም።
2. ከላይ በንኡስ አንቀፅ (1) ላይ የተደነገገው ቢኖርም ወኪሏ በቦታው ያልተገኘችው ሆነ ተብሎ በተቀነባበረ መሰናክል መሆኑ ሲረጋገጥ፣ ወኪሏ ሳትኖር የተከናወነ የምርጫ ተግባር ወኪሏ በምታቀርበው ጥያቄ መሰረት እንደአግባብነቱ በምርጫ ጣቢያው ወይም በምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ይሰጥበታል።

**አንቀፅ 21. <u>የወካዮች ተግባር እና ኃላፊነት</u>**

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ ተወዳዳሪ ምርጫውን በውክልና እንድትታዘብለት የሚወክላት ሰው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ላይ የተጠቀሱ መመዘኛ መስፈርቶችን ማሟላቷን እና የምርጫ ህጉን እና

አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች የምርጫ መመሪያዎች፣ ማንዋሎች እና የአሰራር ስርአቶችን አስመልክቶ ስልጠና የተሰጣት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

**አንቀፅ 22. ውክልናን ስለመሰረዝና ስለመተካት**

1. ማንኛውም ዕጩ ወኪሉን ሊሰርዝና በሌላ ወኪል ሊተካ ይችላል።
2. የማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል ዕጩ ውክልና መሰረዝም ሆነ መተካት የሚችለው የተሰረዘውን ወኪሉን እና ተተኪዉን በፅሁፍ ከምርጫው እለት ሰባት ቀናት በፊት ለምርጫ ክልሉ ሲያሳውቅ ነው።
3. የምርጫ ክልሉ ለሚመለከተው ምርጫ ጣቢያ ነባር ወኪሉ መተካቱን እና አዲስ ወኪል መመደቡን በጽሁፍ ያሳውቃል።
4. ማንኛውም ዕጩ ወኪሉን የለወጠበትን ወይም ያሰናበተበትን ምክንያት እንዲገልጽ አይገደድም።

**አንቀፅ 23. ቅጣት**

ማንኛውም ወኪል በምርጫ ህጉና በዚህ መመሪያ የተደነገገውን ግዴታ ሳይወጣ በመቅረቱ ምክንያት ወይም/እና የምርጫውን ሂደት የሚያውክ ጥፋት የፈፀመ እንደሆነ የወኪልነት መታወቂያው ተሰርዞ በምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ከምርጫ ጣቢያው አካባቢ እንዲርቅ ሊደረግ ወይም አግባብ ባለው ህግ ሊጠየቅ ይችላል።

**አንቀፅ 24. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ለማድረግ የመተባበር ግዴታ አለበት።

**አንቀፅ 25. ተፈፃሚነት የሌላቸው መመሪያዎች እና አሰራሮች**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም አሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

**አንቀፅ 26. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከጥር 21 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ብርቱካን ሚደቅሳ
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ